# የአንድነት ትግሉ ፈር እንዳይስት/ፈር እንዳይለቅ !!

## ከገረመው ሃይሉ( ካርቱም ሱዳን )

የጥቅምት 1998ቱን ህዝባዊና ሰላማዊ አመጽን ወያኔ ከጨፈለቀና የቅንጅት መሪዎችን ካሰረ በኋላ ትግሉ ከመዳከም አልፎ አቅጣጫውን ስቷል። ወያኔ ባደረሰው ፋሺስታዊ ጭፍጨፋ የተነሳ ቁጭትና እልህን አጭሮ የትግል ስልትን አርቅቆ ይበልጥ ለህዝባዊ መነሳሳት መስራት በሚገባ ወቅት የተቃውሞው ጎራ ተዳክሟል። ተከፋፍሏል። ውዥንብር ውስጥ ገብቷል። ጠላትና ወዳጁን መለየት እስኪሳነው ድርስ ዝብርቅርቁ ወጥቷል። ከምንግዜውም ይበልጥ አንድነትና ትብብር በሚያስፈግልበት ወቅት ክፍፍልና ውስጣዊ ሽኩቻ ሰፍኗል። በተለይ በቅንጅት ውስጥ። ተቃዋሚው ለአድርባዮችና አሻግረው የነገዋን ኢትዮጵያ ማየት ለማይችሉ ራእይ አልባዎችና አስመሳይ ታጋዮች በሩን ከፍቷል። ድል ገና ሩቅ ብትሆንም የድል አጥቢያ አርበኞች በዝተዋል። አንዳዶች ደግሞ ከአንዱ የትግል ስልት ወደሌላው ቀኝ ኋላዙረዋል። የትግል ስልት የመርህ ጉዳይ መሆኑ ቀርቶ ባወጣ ያውጣውና እስዎም ይሞክሩት አይነት አድርገውታል። ችግሩ የትግል ስልት መቀያየሩ ላይ ሳይሆን እነዚህ ቀኝ ኋላ የዞሩ ወገኖች ራሳቸውን  ከኢትዮጵያ መሰረታዊ ጠላቶ ኢትዮጵያን የሚያድን እገዛ የመሻታቸው  አጠያያቂነት ላይ ነው።

ትግሉ አቅጣጫ ከመሳቱ  የተነሳ የተቃዋሚ አባላት ነን የሚሉ ወርቃማ ጊዜቸውን በኢንተርኔት የውይይት መድረኮች አማካይነት ስድብ በማወናጨፍ ሲያሳልፉ ማየት አንዱ ምሳሌ ነው። ከአንድ ታጋይ ድርጅት የሚጠበቀው ድርጅታዊ ዲስፐሊን ብሎ ነገር የለም። ይህ እንዳይኖር ደግሞ ድሮውንም በአስመሳይና ታጋዮች የረቀቀ ቅስቀሳ የትግል መሳሪያ የሆኑትን በዘዴ ሸርሽረዋቸዋል። ምሳሌ ልስጥ፦

በህቡእ የመደራጀትን፤ ታጋዮች የሚስጥር ስም የመጠቀምን፤ በህዋስ የመደራጀትን፤ ከብዛት ይልቅ ጥራት ላይ ትኩረት ማደረግን፤ ወዘተ አስፈላጊነት ወደ ጎን ተገፍተዋል። የገዥው ቡድንና የታጋዩ ክፍል ሃይል ባልተመጣጠነበት ሁኔታ ታጋዮች በጠላትም ሆነ በህዝብ መሃል ገብተው ድርጅታዊ ስራቸውን ለመስራት እንቅስቃሴቸውን ከገዢው ቡድን የስለላና የአፈና መዋቅሮች መሰወራቸው ግድ መሆኑ ተዘንግቷል ። የተወሰኑ የታወቁ የተቃዋሚ መሪዎች ማንነታቸው ቢታወቅም ህዝቡ ውስጥ የቀን ተቀን ስራዎችን ሊሰሩ የሚችሉ በተለይም የታች እርከን ታጋዮች ድብቅ መሆናቸው ማለትም በህቡእ መታገላቸው አስፈላጊነት ሆን ተብሎ ይሁን በንዝህላልነት አልታሰበበትም ። አልፎ ተርፎም አንዳድ አላዋቂ ሳሚና የትግሉን ሂደትና የወያኔን አውሬነት ያልተገነዘቡ ህቡእነትን ሲያንቋሽሹ ፤ በህቡእ መስራትን እንደፍርሃት ፤ አልፎም ወንጀል የሚሰሩ ሰዎች የሚጠቀሙበት አሰራር

አስመስለው ሲያቀርቡት አይተናል። በዚህም የተነሳ የአገርቤቱ የተቃዋሚዎች የሁሉም እንቅስቃሴ ማለት ይቻላል በወያኔ የሚታወቅ እንዲሆን አድርጎታል። ያም ወያኔ የፈሪ በትሩን በተቃዋሚው ላይ በሰነዘረበት ወቅት አመች አድርጎለለታል። እነዚህ የዋሆች የሃያላን መንግስታት የስለላ ድርጅቶች አሰራርና አመራሮች ከራሳቸው ህዝብ ሳይቀር የተደበቁ መሆናቸውን እንኳ የሚያውቁ አይመስልም። የኢትዮጵያ ጠላቶች የሆኑት ሻቢያዎችና ወያኔዎች በህቡእ የመታገልን አላስፈላጊነት ቢሰብኩ ባልገረመ ነበር። አስገራሚው የአንድነት የተቃውሞ ጎራ ከሆኑ ወገኖች መምጣቱ ነው። የሚስጥር ስም መጠቀምን እንዲሁ እነዚሁ አላዋቂ ሳሚዎች በማራከሳቸው በሚስጥር ስም መጠቀምን እንደፈሪነት እንዲቆጠር በማድረግ ለወያኔ አመች ጠላት ሆነዋል። ወሳኝ ድርጅታዊ ስራዎችን የሚሰሩ ሰዎችን በሚስጥር ስም ከማስቀመጥ ይልቅ እውነተኛና ሙሉ ስማቸውን ግጥግጥ አድርጎ በመጻፍ የወያኔን ስራ አቅለውለታል። ሳምንት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ አሉ የሚባሉ የተቃዋሚ አባላትን በተለይም የቅንጅት ለዴሞክራሲና ለአንድነት ፓሪቲ አባላትን ለቅሞ የማሰሩና ትግሉ ላይ ከፍተኛ ምት ማድረሱ ከዚህ የተሳሳተ ግንዛቤ የተነሳ ነው። ይህ መጠቀሱ ለማሸማቅ ሳሆን ስህተትን አርሞ ለማይረው ህዝባዊ ትግል የመዘጋጀትን አስፈላጊነት ለማግዘፍ ነው።

አሁን ወዳለንበት ስንመለስ ደግሞ የአንድነትና የዴሞክራሲ ሃይሎች ቅድሚያ ትኩርት የተቃውሞው ጎራ ስህተት ምንነበር? ይህ ስህተት ወደፊት እንዳይደገም ምን መደረግ አለበት? ወያኔን አንኮታኩተን ጥለን አንድነቷ የተጠበቀ ዴሞክራሲያዊ ስርአትና ዘላቂ ሰላም በኢትዮጵያ እንዴት እናሰፍናለን? የተቀማው የህዝብ ድምጽስ እንዴት እናስመልስ?የተቃውሞው ጎራ ትግሉን እንዴት ቢያቀናብር የተሻለ ድል ያስመዘግባል ወዘተ በሚሉ ወቅታዊና ወሳኝ ጥያቄዎች ላይ ነበር መሆን ያለበት። አሁን እንደምናየው በሁሉም ዘንድ ባይባልም እነዚህ ውሳኝ ጥያቄዎች ወደ ጎን ተገፍተዋል።

የትግሉ ማእከል ኢትዮጵያ መሆኗ ቀርቶ አሜሪካና ኢንቴርኔት ሆኗል። ታጋዩ ዘመናዊ የመገናኛ ዘዴዎችንም በብልሃት ትግሉን ለማጎልበት ከመጠቀም ይልቅ ለሽኩቻና ለክፍፍል እየተጠቀሙበት ያሉ ብዙዎች ናቸው። ደግነቱ በአብዛኛው ኢንተርነት ሆነ ፓልቶክ ያው በአውሮጳ አሜሪካ የሚኖሩ ወገኖች መድረኮ ብቻ መሆናቸው ነው። በራስ መተማመን ጠፍቶ አሜሪካና አውሮጳን አንጋጠ መጠበቅ እንዲሁም ደጅ መጥናት ትልቅ የትግል ስልት ከሆነ ሰንብቷል። ባጭሩ መራራውን ሃቅ የመጋፈጥና የሚጠይቀውን መስዋእትነት የሚደፍር ጠፍቷል። ከተቃውሞው ጎራ ገንዘቡን እንኳ ትግሉን በሚጠቅም ሁኔታ ላይ የሚያውል እጅግ አናሳ ነው ቢባል ወደ እውነቱ የተጠጋ ነው። የተቃዋሚ መሪዎችና ድርጅቶች በአውሮጽላን ተጉዘው አገር አቋርጠው በመጓዝ ነጋ ጠባ ስለ ትግሉ ንቃት፤ ማብራሪያና መግለጫ የሚሰጡት እዚያው አውሮጳና በተለይም አሜሪካ ላሉትና ለተማሩት ነው።

ገንዘባቸውን እንዲለግሱ ማባበል በማስፈልጉ ካልሆነ በስተቀር ያ ገንዘብ አፍሪካ ውስጥ በአጎራባቸ አገሮችና ኢትዮጵያ ውስጥ ስንት ስራ ባሰራ ነበር።

ትጥቅ ትግል እንደግፋለን የሚሉ በትጥቅ ትግል ስም የሚነግዱትንና እውነተኛ ታጋዮችን መለየት ያልቻሉ ተሰፊኞች ናቸው። እነዚህኞቹም ወደፊት እንደሚረዱት ሁሉ በስም እንጅ በግብር ለሌሉ ድርጅቶችና ግንባሮች እውቅና ከመስጠት ውጭ ለትግሉ ይህ ነው የሚባል እገዛ እያደረጉ አለመኖናቸውን ገና አላወቁም። የነዚህኞቹ መሳሳት አስገራሚነቱ ሌላ ሳይሆን ፊደል የቆጠሩ ሰዎች የሚያደርጉትን አነስተኛ ጥናትና ምርምር ማድረግ ያልቻሉ መሆናቸው ነው። እውነታውን መጋፈጥና ተገቢዎን መስዋእትነት መክፈል ስለሚከብዳቸው ያላቸው አማራጭ አፈጨሌዎች የሚሉትን ከሩቅ ሆኖ ማድመጥና የሚሉት ማድረግ ብቻ ነው። ይህ ድርጊታቸው ግን ነገ እውነተኛ ታጋዮችን ህዝቡ እንዳያምን የሚያደርግ ትግሉን ወደ ኋላ የሚጎትት መሆኑን አይገነዘቡም። «ከትግሉ ሜዳ በሳተላት ቴሌፎን ኮማንደሩን አነጋገርን» ሲሉ ትንሽ አፋቸውን ያዝ አያደርጋቸውም። አንዳዶች ደግሞ በደመነፍስ በየአቅጣጫው የጦርነት እሳት ቢለኮስ ደስተኞች ናቸው። ይህ በየአቅጣጫው እንዲለኮስ የሚፍልጉት የጦርነት እሳት ግን ኢትዮጵያን መጥቀም መጉዳቱ ላይ አፋቸውን ሞልተው ማስረዳት የሚችሉ አይደሉም። የማድረግ አቅማቸውንም አያውቁም። እናም ትግሉ ፈር እንዳይስት ጥንቃቄ እጅግ ያሻል !!

የቅንጅት ተወካዮች ነን የሚሉም ከቅንጅት ማኒፌስቶ ውጭ የኢትዮያን ልአላዊነት ከማያውቀውና በሻቢያ ከሚዘወረው ኦነግና ኦጋዴንን ለመገንጥል ከሚታገለው የኦጋዴን ነጻ አውጭ ድርጅት ጋር መሰለፋቸው የአንድነት ትግሉን ከፊተኛ ውዥንብር ውስጥ ከከተቱት አንዱ ነው። የወያኔ ፋሺስታዊነት በጥቅምት የ1998 ጭፍጨፋ የተከሰተላቸውና ሰላማዊ ትግል ማለት ከዴሞክራሲያዊ መንግስት ጋር የሚደረግ ትግል መስሏቸው የነበሩ ኢትዮጵያን ማጥፋት አላማየ ነው ካለውና ጸረ ኢትዮጵያ ከሆነው ከሻቢያ እርዳታ ለመሻት ወደ አስማራ ማማተር የውዥምብሩን ጡዘት አመላክቷል።

ለትግሉ መዳከምና በወያኔ ፋሽስታዊ በትር መሽመድመድ ምክንያቱ ከምርጫው ቀደም ባሉት አመታት ተቃዋሚው የተከተለው የትግል መሆኑን አበክሮ መንገር ደግሞ ለቀጣዩ ትግል ስንቅ ነው። ከግንቦቱ 1997 ዓም ምርጫ በተለይም ከጥቅምቱ ጭፍጨፋ በኋላ የተቃውሞ ጎራ ለተከተለውና ላለበት ሁኔታ የድርጅቶችን የማደራጀት ብቃት ያሳየ ነው። ያልዘሩትን ማጨድ እንደማይቻለው ሁሉ የተቃውሞ ጎራም አንጻራዊ ሰላም በነበረበት ወቅት ማድረግ የነበረባቸውን ካለማድረጋቸው የሚቀዳ ነው እቅጩን መንገር ግልጹን ግልጽ ማድረግ እንጅ ሌላ አይደለም። ከሁሉም በላይ በወያኔ ላይ የነበራቸው እሳቤም የሚመነጭ ነው። የሚታገሉት ከአንድ ከውልደቱ እስካሁን ላለፉት ሰላሳ አመታት ሙሉ በሰው ደም እየታጠበ ከመጣ የአረመኔዎች መንጋ ጋር መሆኑን የመዘንጋት ችግር !! ሰላማዊ ትግል

በሚለው ላይም የነበራችው ብቸታም ሌላው ትልቅ ችግር ነው። በጣም መሰረታዊ የሆኑ የአንድ ታጋይ ድርጅት ሊወስዳቸው የሚገባቸውን ቀላል መሰናዶችዎችና ጥንቃቄዎችን ያለማድረግ ስህተቶ ግነው ወጥተዋል። ከላይ የተጠቀሱት በህብእ የመደራጀት አስፈላጊነትን፤ ከአባላት ብዛት ይልቅ በጥራት ላይ ማተኮርን፤ አባላትን በስነ ልቦና ወያኔ ሊያደርስ ለሚችለው አፈና፤ እመቃና ጭፍጨፋ ምንም አይነት ስነልቦናዊ ቅድመ ዝግጅት እንዲያደርጉ አለማዘጋጀት፤ የጸናትን አስፈላጊነት፤ ታግሎ አታጋይ ተኪዎችን የመተካትን አስፈላጊነት፤ የድርጅታዊ ዲስፐሊን አስፈላጊነትን፤ አለማስተማር ሊጠቀሱ ከሚገባቸው ናችው። መስዋት የሚፈልግና ትግሉን የሚቀጥል ሺ በሽህ እያለ ትግሉ የተሽመደመደው በዚህ መሰረታዊ ስህተት ነው ማለት ለቀባሪ አረዱት አይነት ነው። ወያኔ ዋናዋናዎቹን ሲያስርና መግደል ሲጀምር ከህዝቡ መሃል ሆነው ትግሉን የሚያስተባብሩና የሚቀጥሉ በመጥፋታቸው የአብዛኞች በተቃዋሚዎች ተሰፋ ከመቁርጥ አልፈው ራዲዮ ማዳማጥ እንኳ እስከማቆም የደርሱት ተጠቃሽ ናቸው ። በሌላ በኩል ደግሞ ተቃዋሚዎችንና የተቃዋሚ መሪዎችን አይዟችሁ ከጎናችሁ ነን ሲሉ የነበሩ በወያኔ በትር ተሽማቀው ትግል እርም ያሉትን ስናይ ትግሉ ሽርሽር የመሰላቸው ብዙዎችን እንደነበሩ እናያለን።

በትግል አለም መውጣት መውረድ መውደቅ መነሳት ያለ መሆኑን መቀበል ግድ ነው። ግን ሆሌ አንድ አይነት ስህተትን መስራት አለመማርን አመላካች ነውና ካለፉ ስህተቶች መማር ውሳኝ ነው። እታገላለሁ ያለ ሁሉ ስህተት መስራት እንደሚያጋጥመው ሊጠብቀው የሚገባ ጉዳይ ነው። ከበሮ ሲያዩት ያምር ሲይዙት ያደናግር እንደሚባለው ሁሉ የታጋይ ፈተናን የማያውቅ፤ መራብ መጠማትን፤ መታረዝ መበሳቀልን፤ ከሁሉም በላይ በትግሉ ውጣ ውረድ ከራስ ጋር በሚደረግ ውስጣዊ ፍልሚያና ግብግብ ራስን አሸንፎ ጸንቶ ለመታገል ውስጣዊ ሃይል የማፍለቅ ችሎታን የማያውቅ በአስመሳዮችና በአወናባጆች መምታታቱ የታወቀ ነው። ታጋይነት ከቃል ነቢብነት ያለፈ መሆኑን ያማያውቅ፤ ትግል ማለት አንዳፍታ በኢንተርኔት መስኮት ብቅ ብሎ ይህንም ያንነም መወረፍ ለሚመሰው፤ አንድ ኮሚቴ መርቶ የማያውቅ፤ አመት ሁለት አመት ጸንቶ በትግሉ ወላፈን ያልተፈተነ ፤ ፊት ለፊት ከጠላት ጋር ከሚደረግ ግብ ግብ በተጓዳኝ በራስ ድርጅት ውስጥ ሆነ ሌሎች ተቃዋሚዎች ነን ከሚሉ ሊገጥመው የሚችለውን ፈተና ላልተረዳ፤ላላየና ለማያውቅ ትግል ቀላል ነው። እንዲህ አይነቱ በሩቅ ሆኖ ሁሉን ችለው ትግሉን የቀጠሉትና ቀን ከሌት ደፋ ቀና የሚሉት ላይ አነጣጥሮ ሲተች፤ በሰላ ሂስ ሲጠርብ ፤« እኔ ብሆን ኖሮ» ሲልና ሲፎክር መስማት የተለመደ ያለና የሚኖር ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ ወያኔን መታገል ማለት ትግሬን መታግለ የሚስላቸውና የተምታታባቸውም አሉ። የኦነግን ኢትዮጵያን እንደ ቅኝ ገዥ ሃይል የሚያይ ወልጋዳና የተሳሳተ አላማውን መቃወም የኦሮሞን ህዝብ በውስጥ ጉዳዩ ላይ የመወሰን መብቱን እንደመቃወም አድርገው የሚያዩም እንዲሁ የትግሉ ደንቃራዎች ናቸው።

አሁንም ትግሉን ፈር እንዳይስት/እንዳይለቅ ሲባል ኢትዮጵያ ወደየት እያመራች ነው? በሱማሊያ የሚካሄደው የሻቢያና የወያኔ የውክልና ጦርነት ወደየት ያመራናል? የአንድነት ሃይሉ የተቃዋሚ ሚና ምን መሆን አለበት ? በኢትዮጵያ አንድነት የማያማኑ የጎሳ ድርጅቶች በሻቢያ አሰባሳቢነት እየተጠናከሩ መምጣት የሚኖረው አንደምታ ምንድነው?ለዴሞክራሲያዊ ስርዓትና ለአንዲት ሉአላዊት ኢትዮጵያ የሚደረገው ትግል ፈር ስቶ ሌሎች ጠባቦችና ጸረ ኢትዮጵያ ሃይሎች እንዳይጠልፉት የተቃዋሚው ሃይል ቅድሚያ ሰጥቶ መንቀሳቀስ የሚገባው በየትኛው በኩል ነው? ወዘተ በሚሉ ጥያቄዎች ላይ የጠራ አቋም ያስፈልጋል። የተቃውሞው ሃይል አሻግሮ የማየት፤ ከጠላት አንድ እርምጃ ወደፊት የመቀደም፤ ጠላት ባጠመደው ያለመግባት፤ አገራዊ አላማን የማስቀደም አስፈላጊነት፤ ከግርግር የመውጣትን፤ ከስሜታዊነት በራቀ መልክ በማያቋርጥ ሂደት ውስጥ የራስን ሃይልና የማድረግ አቅም ከጠላት ሀይል አንጻር እየመዘኑ ትግሉን መምራት የአንድ ታጋይ ድርጅት አይነታ መለያዎች ሊሆኑ ይገባል ለማለት ነው።

ኢትዮጵያን እግዜር ይጠብቃት !